# የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማስካት እንዲያግዝ ለብሔራዊ ክልላዊ ማንግስታትና ለድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የተመደበው ልዩ የበጀት ድጋፍ አፈፃፀም ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 237/2013

*የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር*

*ጥር/2010*

**የዘላቂ የልማት ግቦችን ለማሳካት እንዲያግዝ ለብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታትና ለድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የተመደበውን ልዩ የበጀት ድጋፍ አፈፃፀም**

**<u>ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 237/2013</u>**

የመጀመሪያው **የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን** ዕቅድ /2003 – 2007/ **አፈፃፀም ከዕቅዱ ዓላማዎች፣ አቅጣጫዎችና ዋናዋና ግቦች አንፃር ተገምግሟል፡፡ በዚህም መሠረት በኢኮኖሚ ዕድገት፣ በመሠረተ ልማት፣ በማህበራዊ ልማት እና በባለብዙ ዘርፎች ዙሪያ ቀጣይነት ያላቸው ስኬታማ ውጤቶች መመዝገባቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡** እንዲሁም **የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ከማሳካት** አንጻርም **በኢኮኖሚ ዕድገትና በማኅበራዊ ልማት ከፍተኛ** ውጤቶች **የተመዘገቡበት ሆኖ ተጠናቋል፡፡ በዕቅዱ የትግበራ ሂደት ቁልፍ በሆኑ ሀገራዊ የልማት ጉዳዮች ዙሪያ ከሀገሪቱ ጫፍ እስከ ጫፍ ከፍተኛ** የሕዝብ **መነሳሳት እና የጋራ የልማት መንፈስ እንደነበረ ታይቷል፡፡** የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድም በዚሁ የአፈጻጸም ግምገማ ላይ በመመሥረት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረግ ጀምሯል፡፡

ይህ የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዋና የልማት አጀንዳ በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የተመዘገቡ ውጤቶችን በማስቀጠል በሀገሪቱ ያለውን ድህነት ማስወገድ ሲሆን፣ ለግብርና እና ለአምራች ኢንዱስትሪው ልማት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ተጨማሪ እሴት እና የሥራ ዕድል በሰፊው እንዲፈጠር ትኩረት በመስጠት የኢኮኖሚ ሽግግርን የማፋጠን ዓላማ ያለው ነው፡፡ በመሆኑም ተግባራዊ የሚደረጉት የልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ዕቅዶች ይህንኑ የልማት አጀንዳ በማሳካት ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡

በመጀመሪያው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን **ዕቅድ የተቀመጡትን** የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦችን ለማሳከት ከ2004 በጀት ዓመት ጀምሮ በፌዴራል መንግስት በተመደበው ልዩ የበጀት ድጋፍ በብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የተለያዩ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ተግባራዊ ሲደረጉ መቆየታቸው ይታወሳል፡፡ እነዚህም ቁልፍ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በግብርና፣ በንጹሕ ውሃ፣ በገጠር መንገድ ግንባታ፣ በትምህርትና ስልጠና፣ በጤና እና በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ዘርፎች ተግባራዊ የተደረጉ ናቸው፡፡ እነዚህን ፕሮግራሞች ለማካሄድ የተመደበውን በጀት ለማስተዳደር የሚያስችል መመሪያም በ2003 ዓ.ም. ተቀርፆ ከ2004 በጀት ዓመት ጀምሮ ተግባራዊ ሲደረግ ቆይቷል፡፡

የሁለተኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድና የዘላቂ ልማት ግቦችን የፖሊሲ ትኩረት መሠረት በማድረግ የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማፋጠን በፌዴራል መንግስት የተመደበው በጀት አጠቃቀም ላይ ለውጥ ማድረግ ተገቢ በመሆኑ፣ የነበረውን መመሪያ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ **በመሆኑም በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማሳካት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር** በ2010 **የበጀት አዋጅ አንቀጽ** 5 **በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈፀሚያ የካፒታል በጀትን አጠቃቀም ለመወሰን የሚከተለውን የተሻሻለ መመሪያ አውጥቷል፡፡**

## 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

***ይህ መመሪያ "የዘላቂ የልማት ግቦችን ለማሳካት የተመደበው የካፒታል በጀት አፈፃፀም ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር*** 237/2013" ***ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡***

## 2. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ:-

2.1. **"ምድብ አንድ" ማለት የትግራይ፣ የአማራ፣ የኦሮሚያ፣ እና የደቡብ ብ/ብ/ሕ መንግስታት ናቸው::**

2.2. **"ምድብ ሁለት" የሱማሌ፣ የሐረሪ ብ/ክ መንግሥታትና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ናቸው::**

2.3. **"ምድብ ሶስት" ማለት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና የጋምቤላ ብ/ክ/መንግሥታት ናቸው::**

2.4. **"ምድብ አራት" ማለት የአፋር ብ/ክ/መንግሥት ነው::**

2.5. **"የክልል መንግሥታት" የሚለው ሐረግ ወይም "ክልሎች" የሚለው ቃል የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርንም ይጨምራል::**

## 3. የልዩ በጀት ድጋፉ ዓላማ

3.1. **የዘላቂ የልማት ግቦችን ለማሳካት የተመደበው** ልዩ የበጀት ድጋፍ የብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት በሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቀመጡትን የዘላቂ የልማት ግቦች ለማሳካት ተግባራዊ የሚያደርጓቸውን ፕሮጀክቶች የካፒታል በጀት ማስፈፀሚያ ብቻ የሚውል ነው፡፡

3.2. የዘላቂ የልማት ግቦች፤ ቀደም በምዕተ- ዓመቱ ግቦች የተካተቱትን የድህነት ተኮር ዘርፎች፤ ማለትም - ጤና፣ግብርና፣ ውሃና ተፋሰስ፣ የትምህርትና ገጠር መንገድ አካቶ በተጨማሪ የአምራች ኢንዱስትሪና የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፎችን በማጣመር የሚተገበሩ ናቸው፡፡

## 4. የልዩ በጀት ድጋፉ አፈፃፀም

4.1. ለክልላዊ መንግስታት የተመደበው ልዩ የበጀት ድጋፍ አፈፃፀም፤ በየክልሎቹ ቅድሚያ ትኩረት ማስጠት ከሚገባቸው ፕሮጀክቶች አንጻር፤ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

4.1.1. በምድብ አንድ ለተመለከቱት የክልል መንግስታት የተመደበው ድጋፍ የሚውለው ለተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ ፕሮጀክቶች ግንባታ ሲሆን፣ የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ ፕሮጀክቶች ግንባታ ዕቅድ እና አፈጻጸም በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተገምግሞ ስምምነት የተደረሰባቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

4.1.2. በምድብ ሁለትና ሶስት ለተመለከቱት የክልል መንግስታት ለምድብ አንድ ክልል መንግስታት ከተፈቀደው በተጨማሪ በልዩ ድጋፉ የሚመደብላቸው በጀት የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማሳካት በሁሉም ዘርፎች የታቀዱ ፕሮጀክቶችን፤ ማለትም - በጤና፣

በግብርና፣ በወሃና ተፋሰስ፣ እና በትምህርትና ገጠር ማገድ ዘርፎች ተጀምረው ላልተጠናቀቁ ነባር ፕሮጀክቶች ቅድሚያ ተሰጥቶ እንዲጠናቀቁ በሚደረግ ቀሪወን በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪ ልማት እና በክለስተር ልማት ዘርፎች አዳዲስ ፕሮጀክቶችን ማስፈፀሚያ የሚውል ይሆናል፡፡

4.1.3. በምድብ አራት ለተመለከተው ክልል የተመደበው በጀት ሙሉ በሙሉ ለውሃና ተፋሰስ ልማት ይውላል::

4.2. የዘላቂ የልማት ግቦች ለማስፈፀም ለክልሎች የካፒታል ወጪዎች የሚደረገው ድጋፍ ጥቅም ላይ የሚውለው የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ከክልሎች ጋር በመመካከር ለሚወስናቸው ዘርፎችና ሚኒስቴር መስርያ ቤቱ በዘረጋው ሥርዓት መሰረት ይሆናል::

4.3. የፌዴራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላት በህግ በተሰጣቸው ሥልጣንና ኃላፊነት መሰረት የዘላቂ የልማት ግቦች ለማሳካት በተመደበው በጀት በክልል መንግሥታት በኩል ለሚካሄዱ ፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞች አፈፃፀም አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው::

# 5. <u>የፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች አፈፃፀም</u>

5.1. በምድብ አንድና ሁለት የተመለከቱት ክልሎች ፕሮግራሞቻቸውን/ ፕሮጀክቶቻቸውን በራሳቸው አቅም የሚፈጽሙ ሆኖ የፌዴራል ሴክተር ሚኒስቴር መስርያ ቤቶች ክትትልና ድጋፍም ይደረግላቸዋል::

5.2. በምድብ ሶስትና አራት የተመለከቱት ክልሎች ከሴክተር ሚኒስቴር መስርያ ቤቶች፤ ለክልሎች ልዩ ድጋፍ ከሚያደርግ የፌዴራል ቦርድ እና ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ድጋፍ ይደረግላቸዋል::

5.3. በምድብ ሁለት እና ሶስት የተመለከቱት ክልሎች የተመደበላቸው በጀት ከዘላቂ የልማት ግቦች፤ ከአገሪቱ አጠቃላይ የልማትና የዕድገት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ጋር በማጣጣም እና ድህነት ተኮር ከሆኑት ዘርፎች፡- ጤና፣ ግብርና፣ ውሃና ተፋሰስ፣ ትምህርትና የገጠር መንገድ ልማት፤ እንዲሁም ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪ እና ከክለስተር ልማት ዘርፎች ጋር በማስተሳሰር የካፒታል በጀት ድልድላቸውን በዘርፎች/በፕሮግራሞች/በፕሮጀክቶች በመለየት አቅርበው ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ጋር በመመካከር ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ይወስናሉ::

5.4. የምድብ አራት ክልል ግን በጀቱን ሙሉ በሙሉ በውሃና ተፋሰስ ልማት ላይ ያውላል::

# 6. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት</u>

6.1. ለዘላቂ የልማት ግቦች የካፒታል ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ በፌዴራል መንግሥት የተመደበውን በጀት ለክልል መንግስታት ያሳውቃል፣

6.2. በምድብ አንድ፣ ሁለት እና ሶስት የተመለከቱት ክልሎች ለካፒታል ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የተመደበላቸውን በጀት በየትኞቹ ዘርፎች/ፕሮግራሞች/ ፕሮጀክቶች ላይ ለማዋል እንደሚፈልጉ በዘርፎች/ በፕሮግራሞች/ በፕሮጀክቶች አጠቃለው ፍላጎታቸውን እንዲያቀርቡ ያደርጋል፣

6.3. በምድብ አራት የተመለከተውን ክልል የውኃና ተፋሰስ ልማት ፕሮግራሞች/ ፕሮጀክቶች የሚያስፈጽመው የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ዕቅዱን እንዲያቀርብ ያደርጋል፣

6.4. ከክልሎች በሚቀርብለት ፍላጐትና ዕቅድ መሰረት ከዘላቂ የልማት ግቦች አንፃር ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገባቸውን ዘርፎች/ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ከሚመለከተው ክልል ጋር በመመካከር መርጦ በመወሰን ለክልሉ ያሳውቃል፣

6.5. የምድብ አራት ክልል ማኅግስት ድጋፍ ሰጪ የሆነው የፌዴራል የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር የክልሉን የጥሬ ገንዘብ ፍላጎት እንዲያቀርብ ያደርጋል፣

6.6. በምድብ አንድ፣ ሁለት እና ሶስት የተካተቱት ክልሎች የጥሬ ገንዘብ ፍላጐታቸውን በወቅቱ እንዲያቀርቡ ያደርጋል፣

6.7. የፕሮግራሞችን/የፕሮጀክቶችን የፊዚካልና የፋይናንስ አፈጻፀም ዕቅድ በመገምገም ገንዘቡን በየሩብ ዓመቱ ለክልሎች ያስተላልፋል፣

6.8. ለክልሎች የተላለፈው ገንዘብ ለታለመለት ተግባር ስለመዋሉ የፊዚካልና የፋይናንስ አፈፃፀም ክትትል፣ ግምገማ እና ድጋፍ ያደርጋል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም ኦዲት ሊያስደርግ ይችላል፣

6.9. የፕሮጀክቶች የፊዚካልና የፋይናንስ ሪፖርቶችን በየሩብ ዓመቱ ከክልሎችና ከፌዴራል አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች እየተቀበለ ይገመግማል፣ የተጠቃለለ ሪፖርት ለመንግሥት ያቀርባል፣

6.10. የፕሮግራሞችን/የፕሮጀክቱን የፊዚካልና የፋይናንስ አፈጻጸም ግምገማ በሚኒስቴር ማስርያ ቤቱ ቀደም ሲል በተቋቋመው የሥራ ክፍል ይከናወናል፣

6.11. ለዘላቂ የልማት ግቦች የተመደበው በጀት ለሌላ የሥራ ፕሮግራም ውሎ ቢገኝ ሚኒስቴሩ ለክልሉ ከሚላክ የፌዴራል መንግሥት የበጀት ድጋፍ ላይ ተቀናሽ አድርጎ ለፌዴራል መንግሥት ተመላሽ ያደርጋል::

## 7. <u>የምድብ አንድ ክልሎች ተግባርና ኃላፊነት</u>

7.1. የምድብ አንድ ክልሎች ዓመታዊ በጀት ሲያዘጋጁ ለተጀመሩ የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ ፕሮጀክቶች ቅድሚያ ትኩረት በመስጠት ለዘላቂ የልማት ግቦች

ማክፈፀሚያ ከተመደበው በጀት ላይ እንደሚሸፈን አድርገው የካፒታል ፕሮግራሞችን/ፕሮጀክቶችን እንዲጠናቀቁ ያደርጋሉ፣

7.2. የተለዩትን ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ዝርዝሩን በማቅረብ በጋራ ምክክር ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ይወስናሉ፣

7.3. በፌደራል መንግሥት ለዚህ ተግባር የተመደበውን በጀት በክልሉ ዓመታዊ በጀት ውስጥ ለብቻ በፕሮግራም/ በፕሮጀክት በመለየት እንዲታወጅ ያደርጋሉ፣

7.4. የፕሮግራሞችን/ፕሮጀክቶችን የፊዚካልና የፋይናንስ አፈጻፀም ዕቅድ ክንውን በየሩብ ዓመቱ በመገምገም የጥሬ ገንዘብ ፍላጎታቸውን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ያቀርባሉ፣

7.5. ለፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ የተላለፈላቸው በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ስለመዋሉ የፊዚካልና የፋይናንስ ዕቅድ ክንውን አፈፃፀም በመከታተል በክልል ካቢኔ በየሦስት ወሩ ግምገማ ያደርጋሉ፣

7.6. የፕሮግራሞችን/የፕሮጀክቶቹን የፊዚካልና የፋይናንስ አጠቃቀም ሪፖርት በየሶስት ወሩ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ያቀርባሉ፡፡

## 8. <u>የምድብ ሁለትና ሶስት ክልሎች ተግባርና ኃላፊነት</u>

8.1. የምድብ ሁለትና ሶስት ክልሎች ዓመታዊ በጀት ሲያዘጋጁ የዘላቂ የልማት ግቦች ለሚያሳኩ የድህነት ዘርፎች፡- ጤና፣ ግብርና፣ ውሃና ተፋሰስ፣ ትምህርት፣ የገጠር መንገድ፤ እንዲሁም የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪ እና የክለስተር ልማት ዘርፎች የሚያስፈልገው ወጪ በፌዴራል መንግሥት ለዚህ ተግባር ተብሎ ከተመደበው በጀት ላይ እንደሚሸፈን አድርገው የካፒታል ፕሮግራሞችን/ፕሮጀክቶችን ይለያሉ፣

8.2. የተለዩትን ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ዝርዝሩን በማቅረብ በጋራ ምክክር ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ይወስናሉ፣

8.3. በፌደራል መንግሥት ለዚህ ተግባር የተመደበውን በጀት በክልሉ ዓመታዊ በጀት ውስጥ ለብቻ በፕሮግራም/በፕሮጀክት በመለየት እንዲታወጅ ያደርጋሉ፣

8.4. የፕሮግራሞችን/ፕሮጀክቶቹን የፊዚካልና የፋይናንስ አፈጻፀም ዕቅድ ክንውን በየሩብ ዓመቱ በመገምገም የጥሬ ገንዘብ ፍላጎታቸውን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ያቀርባሉ፣

8.5. ለፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ የተላለፈላቸውን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ስለመዋሉ የፊዚካልና የፋይናንስ እቅድ ክንውን አፈፃፀም በመከታተል በክልል ካቢኔ በየሦስት ወሩ ግምገማ ያደርጋሉ፣

8.6. በምድብ ሶስት ውስጥ የተመለከቱት ክልሎች የሚመለከታቸው ድጋፍ ሰጪ ሴክተር ሚኒስቴር መስርያ ቤቶች ስለሚያደርጉላቸው ድጋፍ ከሚኒስቴር መስርያ ቤቶቹ ጋር የመግባቢያ ሰነድ ይፈራረማሉ፡፡

8.7. የፕሮግራሞችን/የፕሮጀክቶችን የፊዚካልና የፋይናንስ አጠቃቀም ሪፖርት በየሶስት ወሩ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ያቀርባሉ፡፡

## 9. የምድብ አራት ክልል ማግስት ተግባርና ኃላፊነት

9.1. ዓመታዊ በጀት ሲያዘጋጅ ከእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ጋር በመመካከር የዘላቂ የልማት ግቦች ለሚያሳካው የውሃና የተፋሰስ ልማት የካፒታል ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች የሚያስፈልገውን በጀት በመለየት ወጪው በፌዴራል መንግሥት ለዚህ ፕሮግራም/ፕሮጀክት ተብሎ በተመደበው በጀት እንደሚሸፈን አድርጎ ይለያል፡፡

9.2. ከፌደራል መንግሥት ለፕሮግራሙ/ለፕሮጀክቱ የተመደበውን በጀት በክልሉ ዓመታዊ በጀት ውስጥ ለብቻ ለውሃና ለተፋሰስ ልማት በፕሮግራም/በፕሮጀክት በመለየት እንዲታወጅ ያደርጋል፣

9.3. ለፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ የተላለፈለት በጀት ስራ ላይ ስለመዋሉ የፊዚካልና የፋይናንስ እቅድ ክንውን ክትትልና ግምገማ ከእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ጋር ያከናውናሉ፡፡

9.4. ለሚያከናውናቸው የውሃና ተፋሰስ ልማት ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ የተመደበውን በጀት እንዲያስተዳድር፤ እንዲያስፈፅምና በሥራ ላይ እንዲያውል ለእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ውክልና ይሰጣል፣

9.5. ለተመረጡት የውሃና የተፋሰስ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች የተመደበውን በጀት አጠቃቀም በተመለከተ ከእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ጋር የመግባቢያ ሰነድ ይፈራረማል፣

9.6. የፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች የፊዚካልና የፋይናንስ አጠቃቀም ሪፖርት በየሶስት ወሩ በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር በኩል ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እንዲቀርብ ተገቢውን ድጋፍና እገዛ ያደርጋል፡፡

## 10. ለክልሎች ልዩ ድጋፍ የሚያደርግ የፌዴራል ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት

ለክልሎች ልዩ ድጋፍ የሚያደርገው የፌዴራል ቦርድ ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈፀሚያ ከተመደበው በጀት አፈፃፀም ጋር በተገናኘ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡

10.1. በምድብ ሶስትና አራት የተመለከቱት ክልሎች ለሚያቀርቧቸው ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ዕቅድ አዘገጃጀት፣ አፈፃፀምና ክትትል የተቀናጀ ድጋፍ ይሰጣል፣

10.2. በፌዴራል መንግስት ለክልሎች የተሰጠው የዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈፀሚያ በጀት በተግባር ላይ እንዲውል የማስፈፀም የአቅም ግንባታ እገዛ ያደርጋል፤ ወጤታማነቱን ያረጋግጣል፣

10.3. ከክልሎች ጋር በመሆን በየሩብ ዓመቱ የእቅድ አፈፃፀም ይገመግማል፤ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶችን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ያሳውቃል፣

10.4. የዘላቂ የልማት ግቦችን ለማሳካት ሊደረግ በሚገባው ድጋፍ ላይ በሚወያይበት ጊዜ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴርን በቦርድ ስብሰባ ላይ እንዲገኝ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 11. የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት

ሚኒስቴሩ ለሌሎች ክልሎች የሚሰጠው ክትትልና ድጋፍ እንደተጠበቀ ሆኖ የምድብ አራት ክልል የዘላቂ የልማት ግቦችን ለማሳካት ከሚያደርገው ጥረት ጋር በተያያዘ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

11.1. የውሃና ተፋሰስ ልማት ፕሮግራሞችን/ፕሮጀክቶችን ከክልሉ ጋር በመመካከር ለይቶ ዝርዝሩን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ያቀርባል፣

11.2. በክልሉ ለሚከናወኑት የውኃና ተፋሰስ ልማት ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የተመደበውን በጀት ከክልሉ በሚሰጠው ውክልና መሰረት ያስተዳድራል፣ ያስፈጽማል፣

11.3. የፕሮግራሞችን/ፕሮጀክቶችን የፊዚካልና የፋይናንስ እቅድ ክንውን በመገምገም የክልሉ የጥሬ ገንዘብ ፍላጎት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ያቀርባል፤

11.4. በክልሉ የሚከናወኑትን የውሃና ተፋሰስ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ይከታተላል፣ ይገመግማል፤ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ፣ ለክልሉ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ እና ለመስኖና ተፋሰስ ልማት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት በየሶስት ወሩ የፊዚካልና የፋይናንስ አፈፃፀም ሪፖርት ያቀርባል፣

11.5. ከፕሮግራሞች/ከፕሮጀክቶቹ አፈፃፀም ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ጋር በየወቅቱ ምክክር ያደርጋል፣

11.6. በዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈፀሚያ በጀት የሚከናወኑትን የውሃና ተፋሰስ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች አተገባበር በተመለከተ ከክልሉ ጋር የመግባቢያ ሰነድ ይፈራረማል፡፡

## 12. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት

12.1 በምድብ አንድ የተመደቡ ክልሎች የሚቀርቡትን የፊዚካልና የፋይናንስ ዕቅድ ከገመገመ በኋላ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ጋር በጋራ በመወያየት የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች የግንባታ ፕሮጀክቶች እንዲፀድቁ ያደርጋል፡፡ የየሩብ ዓመት የፕሮጀክቶች አፈፃፀም በዝርዝር እንዲቀርብ በማድረግ ክልሎች በተገኙበት ይገመግማል፡፡ የፕሮጀክቶችን አፈጻጸም ይከታተላል፣ ሪፖርትም ለመንግሥት ያቀርባል፡፡

12.2 የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ግንባታ ፕሮጀክቶች የፊዚካልና የፋይናንስ ዕቅድ እንዲሁም አፈፃፀም የሚገመግም የሥራ ክፍል ያቋቁማል፡፡

12.3 የዘላቂ የልማት ግቦችን ለማሳካት በሚመደበው ልዩ የበጀት ድጋፍ የሚከናወኑ የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች የግንባታ ፕሮጀክቶችን የሥራ ማስኬጃ ወጪዎችን ለአንድ ጊዜ አጥንቶ በማቅረብ ያስወስናል፡፡

## 13. የሌሎች ሚኒስቴር መ/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት

13.1 ጉዳዩ የሚመለከታቸው የፌዴራል መንግሥት መስርያ ቤቶች እንደሚመረጠው ፕሮግራም/ፕሮጀክት ዓይነት ለክልል መንግሥታት በተናጠል የማስፈፀምና ድጋፍ የመስጠት ኃላፊነት ይኖርባቸዋል።

13.2 የሚያከናውኑት የማስፈፀምና ድጋፍ የመስጠት ተግባር እንደ ፕሮግራሙ/ ፕሮጀክቱ ዓይነት ተጣጥሞ በዚህ መመርያ አንቀፅ 11 ስር ለእርሻና የተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር በተሰጠው አኳኋን ይከናወናል።

13.3. ለክልል መንግሥታት ስለሚሰጡት ድጋፍ ከክልል መንግሥታት ጋር የመግባቢያ ሰነድ ይፈራረማሉ።

## 14. ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈፀሚያ የተመደበው በጀት የፋይናንስ አስተዳደር

14.1. ለዘላቂ የልማት ግቦች የተመደበው በጀት የሚመራው በመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች መሠረት ይሆናል።

14.2. ማናቸውም ለዚህ ለተግባር የሚከናወኑ ግዥዎች በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅና መመሪያ መሠረት ብቻ የሚፈፀሙ ይሆናል።

14.3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገው ቢኖርም፣ በምድብ አንድ ከተሟከቱት የክልል መንግስታት በስተቀር፣ ሌሎች ክልሎች የክልላቸው የገበያ ዋጋን መሠረት በማድረግ በክልሉ መንግሥት፣ በሌሎች ክልሎች ወይም በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት ሥር ከሚገኙ የልማት ድርጅቶች ዕቃና አገልግሎቶችን ግዥ ከአንድ አቅራቢ በሚፈፀም የግዥ ዘዴ መፈፀም ይችላሉ።

14.4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 መሠረት ዕቃና አገልግሎቶችን ግዥ ከአንድ አቅራቢ በሚፈፀም የግዥ ዘዴ ሲፈፀም፣ የሴክተር ቢሮ የውስጥ ኦዲት፣ የክልሉ ዋናው

ኦዲተርና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ደግሞ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በሚያከናውኑት ኦዲት ግዥው የተፈፀመው በገበያ ዋጋ መሠረት መሆኑን ያጣራሉ፡፡

14.5. በገጠር መንገድ ግንባታ ሥራ የሚሰማሩ አነስተኛ የሥራ ተቋራጭ ድርጅቶች የመሣሪያ ችግር ያለባቸው መሆኑ ከተረጋገጠ የክልሉ መንግሥት ሥራውን ለማቀላጠፍ ሲባል አስፈላጊነታቸው የታመነባቸውን የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ብቻ በክልሉ የትራንስፖርት ቢሮ/የገጠር መንገዶች ባለሥልጣን እንዲገዙ በማድረግ ተቋራጮቹ በሊዝ መልክ የመሣሪያዎቹን ዋጋ እየከፈሉ ዋጋውን ከፍለው ሲያጠናቅቁ የመሣሪያው ባለቤት የሚሆኑበትን ሥርዓት ወይም በህጉ መሠረት በሚሰጣቸው የቅድሚያ ክፍያ (advance) መሣሪያዎቹን እንዲገዙ ወይም ለባንኮች ዋስትና በመስጠት ለማሽነሪዎቹ መግዣ የሚውል ብድር እንዲያገኙ ለማድረግ ይችላል፡፡

## 15. የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር

15.1. የዘላቂ የልማት ግቦችን ለማሳካት እንዲቻል ለዘጠኝ ክልሎችና ለድሬዳዋ አስተዳደር ለካፒታል ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ ብቻ የሚውል በፌዴራል መንግሥት የበጀት ድጋፍ ይደረጋል፡፡

15.2. በጀቱ ለክልሎች የተደለደለው የፌዴሬሽን ምክር ቤት ባፀደቀው ቀመር መሠረት ነው፡፡

15.3. የክልል መንግሥታት የዘመኑን በጀት ዓመት በጀት ሲያዘጋጁ የዘላቂ የልማት ግቦችን የሚያሳኩ የካፒታል ፕሮግራሞችን/ፕሮጀክቶችን በመለየት ወጪው ከፌዴራል መንግሥት ለዚህ ፕሮግራም/ፕሮጀክት ተብሎ ከተመደበው በጀት ላይ እንደሚሸፈን በማድረግ በሴክተር ቢሮዎችና በዘርፍ/ በፕሮግራም/ በፕሮጀክት በመለየት ያውጃሉ፡፡

15.4. ለፕሮግራሞቹ/ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ ለክልሎች የሚተላለፈው በጀት የልማት ፕሮግራሞቹን/ፕሮጀክቶቹን የፊዚካልና የፋይናንስ እቅድና አፈፃፀም መሰረት በማድረግ ነው፡፡

15.5. የዘላቂ የልማት ግቦች ለማሳካት በተያዙ ዘርፎች/ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች መካካል የሚደረገው የበጀት ዝውውር የመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎችን ተከትሎ መፈፀም አለበት፡፡

15.6. የፀደቀውን የበጀት ድልድል ከተፈቀደለት ሴክተር ወደ ሌላ ሴክተር ለመቀየር የሚቻለው የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ስምምነት ሲገኝ ብቻ ይሆናል፡፡

## 16. የገንዘብ ፍሰትና የክፍያ አፈጻጸም

16.1. ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈፀሚያ ለክልሎች ለተመደበው በጀት ማንቀሳቀሻ የክልል መንግሥታት ለምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች የተከፈተውን የተለየ የባንክ ሂሣብ ይጠቀማሉ፡፡

16.2. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ከክልል መንግሥታት በሚቀርበው የፊዚካልና የጥሬ ገንዘብ እቅድ መሠረት የመጀመሪያውን ክፍያ ለክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ለዚሁ ተብሎ በተከፈተው የባንክ ሂሣብ ያስተላልፋል፡፡

16.3. በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ የተላለፈው ገንዘብ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በየሩብ ዓመቱ የፊዚካልና የፋይናንስ አፈፃፀም ሪፖርት ሲቀርብለት፣ ሪፖርቱን በመገምገም ተጨማሪ ገንዘብ ለክልሎች ይልካል፡፡

16.4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 በተገለፀው መሠረት የፊዚካልና የፋይናንስ ሪፖርት ሳይቀርብ ክፍያ አይተላለፍም፡፡

16.5. ገንዘቡ የሚተላለፈው ለተግባሩ ገንዘብ ማንቀሳቀሻ በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ሲሆን የሥራውን የበጀትና የገንዘብ አጠቃቀም ለማወቅና ከሌሎቹ ሥራዎች ለመለየት የተለየ ሌጀር ተዘጋጅቶ የበጀቱ ገቢና ወጪ በዚህ ሌጀር ላይ ይመዘገባል፡፡

16.6. በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በየክልሉ ለዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈፀሚያ ከተላለፈው ገንዘብ ውስጥ በሥራ ላይ ያልዋለ በባንክና በሳጥን የሚገኝ፣ እንዲሁም ለችሮታ ጊዜ ክፍያ ተላልፎ ክፍያ ሳይፈፀም የቀረ ገንዘብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ፈሰስ ይደረጋል፡፡

16.7. የበጀቱ ክፍያ የሚፈፀመው የመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች እንዲሁም የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅና መመሪያዎች ተጠብቀው ይሆናል፡፡

## 17. የሂሣብ አመዘጋገብና ሪፖርት አቀራረብ

17.1. ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈፀሚያ የተመደበው በጀት ምንጩ ከመንግሥት ግምጃ ቤት በመሆኑ የሂሳብ አሠራሩ የመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች እንዲሁም በሥራ ላይ ያሉትን የሂሣብ አያያዝ ሥርዓቶች ተከትሎ የሚፈፀም ይሆናል፡፡

17.2. ለዘላቂ የልማት ግቦች ተግባራዊ ለሚደረጉ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ የሚተላለፈውን ገንዘብ አስመልክቶ መደበኛውን የሪፖርት ማቅረቢያ ቅፆች በመጠ ቀም በየሶስት ወሩ የሂሳብ ሪፖርት ተለይቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ይቀርባል፡፡

17.3. ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት ከሌሎች መደበኛ ሂሳብ ሪፖርቶች ጋር ተጠቃሎ ከተዘጋጀ በኋላ የዘላቂ ልማት ግቦች ዓመታዊ ሂሳብ ተለይቶ በክልሉ ዋና ኦዲተር እንዲመረመር ይደረጋል፡፡

## 18. ኦዲት

18.1. ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈፀሚያ ለየክልሉ የተመደበው በጀት ዓመታዊ ሂሣብ ለየብቻው ተለይቶ በየክልሉ ዋና ኦዲተር ይመረመራል፤ የኦዲት ሪፖርትም ተጠቃሎ ኮፒው ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ይላካል፡፡ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴርም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሂሳቡን ኦዲት ሊያስደርግ ይችላል፡፡

18.2. የእያንዳንዱ ክልል ሴክተር ቢሮዎች የውስጥ ኦዲት በጀቱ በሴክተር ቢሮው ላይ ተይዞ የሚተገበረውን የዘላቂ የልማት ግቦች ፕሮግራም/ፕሮጀክት ሂሣብ በየሦስት ወሩ ይመረምራል፤ የሪፖርቱንም ኮፒ ለክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ያስተላልፋል፡፡ የክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮም ሪፖርቱን በማጠቃለል በየሩብ ዓመቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ያቀርባል፡፡

18.3. ለዘላቂ የልማት ግቦች የተመደበው በጀት ለሌላ የሥራ ፕሮግራም ውሎ ቢገኝ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ለክልሉ ከሚላክ የፌዴራል መንግሥት የበጀት ድጋፍ ላይ ተቀናሽ አድርጐ ለፌዴራል መንግሥት ተመላሽ ለማድረግ እንዲችል የሴክተር መስርያ ቤቱ የውስጥ ኦዲት ይህንን በየጊዜው ተከታትሎ ለክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሪፖርት ያደርጋል፡፡

## 19. ያልተፈቀዱ አፈፃፀሞች ወይም ክልከላ

19.1. ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈፀሚያ የተመደበውን የፕሮግራሙን በጀት ከሌሎች የክልሉ በጀት ጋር በመቀላቀል ስራ ላይ ማዋል አይቻልም፡፡

19.2. ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈፀሚያ ለክልል መንግሥታት የተመደበውን በጀት በምክክር ከተወሰኑት ፕሮጀክቶች ውጭ ላሉ ለሌሎች ነባር የካፒታል ፕሮጀክቶች፣ ለአዲስ ፕሮግራሞች እና ለመደበኛ ሥራዎች ማዋል አይቻልም፡፡

19.3. ለዘላቂ የልማት ግቦች ለየክልሉ የተመደበው በጀት በክልል ደረጃ ተይዞ በክልሉ ውስጥ ለተመረጡት ዘርፎች/ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች በሥራ ላይ ከሚውል በስተቀር ለወረዳዎች ተከፋፍሎ አይደለደልም፡፡

19.4. በጀቱ በመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደርና የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ህጐች የሚመራ በመሆኑ ገንዘቡን እነዚህ ህጐች ከሚያዙት ውጪ በብድር

መስጠት አይቻልም፡፡

## 20. የተሻረ መመሪያ

የምእተ ዓመቱን የልማት ግቦች ለማሳካት እንድያግዝ ለብሔራዊ ክልላዊ መንግስታትና ለድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የተመደበው ልዩ የበጀት ድጋፍ አፈፃፀም ለመወሰን ሐምሌ 06/2003 ዓ.ም የወጣው መመሪያ ተሽሮ በዚህ መመሪያ ተተክቷል፡፡

## 21. የመመሪያው ተፈፃሚነት

ይህ መመሪያ ከጥር 25 ቀን 2010 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጥር 25 ቀን 2010 ዓ.ም

ዶ/ር አብርሃም ተከስተ
የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስትር

ማሳሰቢያ፣ ለአፈፃፀም የሚረዱና የዚህ መመሪያ አካል የሆኑ አራት ቅጾች ከዚህ ጋር ተያይዘዋል፡፡

## 22. ልዩ ልዩ ቅፆች

**ቅጽ 1፡ ከክልሎች የፕሮግራሞች/የፕሮጀክቶች ዝርዝርና የበጀት ጥያቄ ማቅረቢያ**

**ክልል/ከተማ አስተዳደር __________________________________________**

**በ '000 ብር**

| ተ.ቁ | ዘርፍ/ፕሮግራም/ፕሮጀክት | ለ ---------- በጀት ዓመት የተጠየቀ በጀት | መግለጫ |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

*ያዘጋጀው ስም ---------------------------* *ጥያቄውን ያፀደቀው ስም ------------------*

*ሃላፊነት---------------------------* *ሃላፊነት---------------------------*

*ፊርማ ---------------------------* *ፊርማ---------------------------*

*<u>ማሳሰቢያ</u>፣ ይህ የፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ዝርዝርና የበጀት ጥያቄ በክልሉ/ከተማው ካቢኔ መጽደቅና ማህተም መደረግ አለበት፡፡*

## ቅጽ 2፡ የፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የፊዚካልና የፋይናንስ ዕቅድ ማቅረቢያ

ክልል/ ከተማ አስተዳደር ________________________________

| ተ/ ቁ. | ዘርፍ/ፕሮግራም/ፕሮጀክት | የጸደቀ በጀት (በሺ ብር) | የፊዚካል ዕቅድ በ% | | | | የፋይናንስ ፍላጎት (በሺህ ብር) | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |

## ቅጽ 3፡ የፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የፊዚካልና የፋይናንስ አፈጻጸም ማቅረቢያ

ክልል/ ከተማ አስተዳደር ______________________________

| ተ/ ቁ. | ዘርፍ/ ፕሮግራም/ ፕሮጀክት | የፀደቀ በጀት (በሺህ ብር) | የ______ሩብ ዓመት የፊዚካል ሥራዎች በመቶኛ | | እስከአሁን የተከናወኑ የፊዚካል ሥራዎች በ% | የፋይናንስ አጠቃቀም በ_____ሩብ ዓመት /በሺህ ብር/ | | እስከአሁን የወጣ ገንዘብ /በሺህ ብር/ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንወን | | ዕቅድ | ክንወን | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |

ቅጽ 4፡ የ________በጀት ዓመት የጥሬ ገንዘብ ዕቅድ አፈጻጸም ማቅረቢያ

ክልል/ ከተማ አስተዳደር ______________________________

በሺህ ብር

| ተ/ ቁ. | ዘርፍ/ፕሮግራም/ፕሮጀክት | የጸደቀ በጀት የዓመት | እስከአሁን የተላለፈ | እስከአሁን ሥራ ላይ የዋለ | እስከአሁን ሥራ ላይ ያልዋለ | ለ__________ሩብ ዓመት የሚያስፈልግ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |